**ያቁሙ**

# ኤሮሶል አፈጣጠር ሂደቶች (AGP)

## በመካሄድ ላይ

**ለምንም ጎብኚዎች አይፈቀዱም።**

## ከመግባትዎ በፊት፡

- እጅን ይታጠቡ ወይም ይቀቡ
- ጭንብል ይልበሱ
- ጋዎንና ጓንት ያድርጉ ዓይን መከላከያን
- ይልበሱ የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር

ለሕመምተኛ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ሊጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።

የጋራ መገልገያዎችን በፀረ ተባይ ያጽዱ።

*ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ በEnvironmental Services (አከባቢ አገልግሎ) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።*

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH

7/30/2024

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ታካሚው ከወጣ፣ ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኃላ ምልክቱን ያንሱ።**

# ኤሮሶል አፈጣጠር ሂዴቶች (AGP)

## የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)

***በመደበኛ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሠረት ለሎች የግል መከላከያ መሣሪያውች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የግል መከላከያ መሣሪያዎች በመያዝ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ለሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማሳያዎች ናቸው።***

| ***የግል መከላከያ መሣሪያዎች (ልገሳ) ማድረግ።*** | ***የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማውለቅ*** |
|---|---|
| **1.** የእጅ ንፅህናን ያከናውኑ<br>**2.** መከላከያ ጋዎን፣ አስተማማኝ የሆነ ጥምጣም/ከረባት ያድርጉ<br>**3.** መተንፈሻ ወይም የፊት ጭምብል ማድረግ፣ ተስማሚና በትክክል መግጠማቸውን ማረጋገጥ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ<br>**5.** ጓንቶችን ያድርጉ | **1.** ከታካሚ ክፍል ውስጥ ከሆናችሁ፣ እጅን በማይበክል መልኩ ጓንቶችን ያውልቁ።<br>**2.** ጓንት ያውልቁ፥ ከረባት/ጥምጣም ይፍቱ፣ ሊጣሉ ለሚችሉ ጋዎኖች ማሰሪያ የሚውል ከሆነ ከረባቱን ይቁረጡ። እያንዳንዱን ክንድ ለማስወገድ አንድ ትከሻን በአንድ ጊዜ በመያዝ ያስወግዱ። ካወለቃችሁ በኃላ በመጠቅለል ትክክለኛ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ። አሁን ከክፍሉ መውጣት ትችላላችሁ።<br>**3.** እንደወጣችሁ፣ የእጅዎን ንጽሕና (የሚታይ ቆሻሻ፣ የሰገራ ንክኪ ወይም ከቅድመ-ጥንቃቄ መጓደል ንክኪ አጋጥምዎት ከሆነ፣ ሳሙና ውኃ ይጥቀሙ) ያከናውኑ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ/መነጽር ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለሚችል የዓይን መከላከያ መጀመሪያ ክፍል አይንኩ።<br>**5.** መተንፈሻ/የፊት ጭምብል በትክክል በመያዝ ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለምችል የፊት ለፊት ክፍል ከመንካት በመቆጠብ እንዳይበክል አድርገው ተገቢ በሆነ መልኩ ይጣሉ።<br>**6.** የእጅዎን ንፅህና ደጋግመውይጠብቁ። |

### እንደ የሚከተሉት ሁኔታዎች ለመጠቀም፡- (የተቋሙን ፖሊሲ ይመልከቱ)

- እንደ ተቋሙ ፖሊሲ ከሆነ ብዙ-መድኃኒት ተቋቋሚ ኦርጋኒዚሞች (MDRO)ና የኢፒደሚኦሎጂካል ፓቶጀንስ ጉዳይ
- እከክ/ቅማል
- ያለማቋረጥ ፈሳሽ የሚያፈስ ቁስል/የመግል ቁስል

### የታካሚ ምደባ

- ታካሚን የግል ክፍል ወስጥ ይመድቡ። የማይገኝ ከሆነ፣ ለጋራ መገልገያ መመሪያዎችን ይከተሉ።

### ምግቦችና ዕቃዎች

- ልዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። የማዕድ ቤት ዕቃዎች ዕቃ ማጠቢያ ውስጥ ይጠቡ።

### የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ

- አልጋ ልብስ ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ። ከመጠን በላይ ንክኪና አልጋ ልብስ ማራገፍን ያስወግዱ። ለባዮአዛርድ ቆሻሻ፣ ምድብ ቢ የህክምና ቆሻሻ መመሪያዎችን ይከተሉ።

### ክፍልን ማጽዳት

- ተገቢ ከሆነ የአየር ዝውውር በኃላ በሆስፒታሉ አሠራር መሠረት የግል መጋረጃ ቅየራ ጨምሮ መደበኛ የጽዳት ሂደቶች ይካሄዳሉ።

### መሣሪያና አቅርቦቶች

- ክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይቀመጡ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

### ትራንስፖርት

- የታካሚውን የመውጫ ቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታ ለተቀባይ ክፍል ማሳወቅ።
- ታካሚው እጁን መታጠብ አለበት። ታካሚው ጋዎን ወይም ንጹህ አንሶላ እንዲለብስ ማድረግ እና በበሽታ የተጎዱ ቦታዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ማሸግ(ለምሳሌ ክፍት/ፈሳሽ ያለው ቁስል)
- አጓጓዥ ከታካሚው ክፍል ከመውጣቱ በፊት እጁን መታጠብና የግል መከላከያ መሣሪያ ያወጣል። በመጓጓዣ ጊዜ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠበቅ ከሆነ ተገቢውን PPE ይልበሱ
- የትራንስፖርት መኪናን ፀረ-ተባይ በመርጨት ያጽዱ።

***በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ቅድሙ ጥንቃቄ ያቋርጡ፡***

***ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ በEnvironmental Services (አከባቢ አገልግሎ) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።***

**420-583 April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

Washington State Department of HEALTH

9/23